

2025-2026

# የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ ስነምግባር ደንብ/ኮድ

የፌዴራል እና የስቴት ሕጎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ፖሊሲ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተዳደራዊ ደንቦች እና ሌሎች መመሪያዎች ሊለወጡና እና በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን መግለጫዎች እና ማጣቀሻዎች ሊተኩ ይችላሉ።

የተማሪ ስም ______________________________

ስልክ ______________________________

Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

### ዕሴት፡-

ትምህርት
መከባበር
መልካም ግንኙነት
ልህቀት/ምጡቅነት
ፍትኃዊነት

### ራእይ፡-

የወደፊት ዝግጁነት፡-
በተለዋዋጭ አለም ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ለእድገት፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ፣ እና ለስኬታማነት ዝግጁ ሆነው ይመረቃሉ—በማህበረሰባቸው ውስጥ እና ከዚያም በላይ ለመሪነት፣ ለአገልግሎት፣ እና በጎ ተጽእኖ ለመፍጠር በሚያስችላቸው እውቀት፣ ችሎታ፣ እና በራስ በመተማመን ተገንብተው ይመረቃሉ።

### ተልእኮ፡-

እምቅ አቅምን በተግባር እንዲገለጥ ማድረግ፥
ሁሉም ተማሪዎች ጥልቅ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ፣ ትምህርትን የማዳበር እና የማበልጸግ እድሎችን በመጠቀም ጠንካራ የአካዳሚክ መሠረት ይኖራቸዋል።
ሁሉም ተማሪዎች ለውጦችን እና አዳዲስ ሁኔታዎችን መቋቋም የሚችሉ ሆነው ዕድሜ ልክ የመማር ፍላጎትና ጽናትን ያዳብራሉ።
ሁሉም ተማሪዎች ትርጉም ባለው ግንኙነት ላይ የተመሠረተ መስተጋብር፤ ውጤት ላይ የሚያተኩሩ እና በትብብር የሚሠሩ ይሆናሉ። ሁሉም ተማሪዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ አዎንታዊ ተጽእኖ ለመፍጠር የተዘጋጁ፤ እና በግል ህይወታቸው እና በሙያዊ ብቃታቸው ለስኬታማነት የሚተጉ ይሆናሉ።


**የትምህርት ቦርድ**
Board of Education

**ሚ/ስ ጁሊ ያንግ** Ms. Julie Yang
**ፕሬዚደንት** President

**ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን** Ms. Grace Rivera-Oven
**ም/ፕሬዚደንት** Vice President

**ሚ/ስ ሪታ ሞንቶያ** Ms. Rita Montoya

**ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ** Ms. Karla Silvestre

**ወ/ሮ ላውራ ስቲዋርት** Mrs. Laura Stewart

**ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ** Ms. Brenda Wolff

**ሚ/ስ ናታሊ ዚመርማን** Ms. Natalie Zimmerman

**ሚ/ስ አኑቫ ማሎ** Ms. Anuva Maloo
**ተማሪ አባል** Student Member

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
Montgomery County Public Schools

**ቶማስ W. ቴይለር (ዶ/ር)**
**የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት**
Thomas W. Taylor, Ed.D., M.B.A.
Superintendent of Schools



15 West Gude Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org


## ማውጫ


ፈጣን የማጣቀሻ/የማመሳከሪያ መመሪያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ክፍል 1፡- ባህሪ እና የደህንነት ፍልስፍና . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ክፍል 2፡- የባህሪ ማስተካከያ ጣልቃ ገብነት ሜትሪክስ (Behavior Intervention Matrix) . . 4

በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6

የተማሪ ባህሪያት እና ጣልቃገብነት የምላሽ አሰጣጥ ደረጃ ሜትሪክስ . . . . . . . . . . .12

ስለ ባህሪ ጣልቃገብነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .26

ስለ ተማሪ ባህሪ ጣልቃገብነት፣ ሠላም፣ እና ደህንነትን በተመለከተ የትምህርት ቦርድ "BOE" ፖሊሲዎች እና የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች. . . . . . . . . .29


የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ በጀርባ ሽፋን ገጽ ላይ ይገኛል
(ድርጅታዊ ሠንጠረዥ ሲሞላ እና ሲጸድቅ የግንኙነት መረጃ ወቅታዊ መሆን እንዳለበት በህግ የተደነገገ ነው)

# ፈጣን መረጃ ለማግኘት የሚጠቅም መመሪያ
# የተማሪዎች መገልገያዎች/ሪሶርሶች

## በቀውስ ግዜ ክፍት የስልክ መስመር
**24-ሰዓት መረጃ መስጠት፣ሪፈራል፣ እና በውይይት መርዳት**

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማዕከል**
Hotline/EveryMind/ . . . . . . . . . . . . . 988
እና https://www.every-mind.org/
በይነመረብ ላይ የሚያነጋግሩ ሰዎች ያሉበት እና የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፥ 24 ሰዓት የማወያየት አገልግሎት ይሰጣል።

Montgomery County Crisis Center - 240-777-4000

ሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማእከል
ቀውስ ማዕከል የአእምሮ ጤና ችግር ላጋጠማቸው ግለሰቦች 24/7 ነፃ የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል።

Trevor Project . . . . . . . 866-488-7386፣ Text 678 678

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ወጣቶች ድንገተኛ የስልክ ጥሪ መስመር፡-**
Youth Crisis Hotline of Montgomery County 988
በሰለጡኑ ካውንስለሮች አማካይነት 24 ሰዓት በስልክ የማማከር ድጋፍ እና ሪፈራል የምስጢር አገልግሎት ይሰጣል።

## የደህንነትና የፀጥታ አስጊ ሁኔታዎችን ሪፖርት ለማድረግ፡-

MCPS የደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ ማኔጅመንት ክፍል . 240-740-3066
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችን እና ጽ/ቤቶችን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው ቢሮ።

MCPS የተማሪ ምግባር እና ይግባኝ SCA@mcpsmd.org ወይም TitleIX@mcpsmd.org . . . . . . . . . . 240-740-3215
MCPS ዲስትሪክት አቀፍ Title IX አስተባባሪ እና ዲስትሪክት አቀፍ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነትን የሚመለከት ግንኙነት ሃላፊ። የተማሪ ስነምግባር እና ይግባኝ (SCA) ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡- www.montgomeryschoolsmd.org/compliance/ SCA ከትምህርት ቤቶች፣ ከህግ አገልግሎት ክፍል፣ እና ከሌሎች የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች እና ከማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር የፖሊሲዎችን፣ የደንቦችን እና የመመሪያዎችን አፈፃፀም ወጥነት ለማረጋገጥ ከሰብአዊ የግንኙነቶች ክፍል ጋር በማቀናጀት ይሰራል። ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ (ታይትል IX ጾታዊ ትንኮሳ ጭምር) እና ማስፈራራት፣ የልጅ ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ፣ ጥላቻ፣ አድሎአዊነት፣እና የተማሪ ጾታ ማንነት ክስተቶችን በሚመለከት አፈጻጸሙና ትግበራው ወጥነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ይሠራል።

MCPS Cyber Safety dropbox:- . CyberSafety@mcpsmd.org
MCPS ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ኦንላይን እንቅስቃሴን ሪፖርት ማድረጊያ Dropbox።

ከኮምፒተር ኔተዎርኮች ጋር ስለተገናኙ ጉዳዮች የጥቆማ መስመር - Cyber Tipline . . . . . . . . . . . . . . . 1-800-843-5678
24/7 ልጆችን ለወሲብ ድርጊት በማባበል የተጠረጠሩትን ሪፖርት ለማድረግ የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፣ ከቤተሰቦቻቸው ውጪ የሚፈፀሙ ወሲባዊ ድርጊቶች፣የህፃናት ፖርኖግራፊ፣የህፃናት ወሲባዊ ቱሪዝም፣የህፃናት የወሲብ ንግድ፣ለልጆች የሚላኩ ያልተጠየቁ ጸያፍ ቁሶች፣የተሳሳተ/የተጭበረበሩ የተጠቃሚ ስሞች እና አሳሳች ቃላትን ወይም በኢንተርኔት ላይ የሚለጠፉ ዲጂታል ምስሎችን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 የሚያገለግል የስልክ መስመር።

Safe Schools Maryland Hotline . . 833-MD-B-Safe (833-632-7233)
ደህንነታቸው የተጠበቀ የሜሪላንድ ት/ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ መስመር 24/7 ስም ሳይገለጽ ነፃ የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለጠቅላላው ማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ጉዳዮችን ጨምሮ ማንኛ ውንም የት/ቤት ወይም የተማሪ ደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል። ስልክ የሚደውለውን ሰው ማንነት በመደበቅ ስለተፈጠረው ክስተት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አግባብ ካላቸው ቢሮዎች ጋር መረጃ ይጋራል።

Montgomery County Child Protective Services, Department of Health and Human Services
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎት፣ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት
(24 ሠዓት ክፍት የስልክ መስመሮች) 240-777-4417 ወይም 240-777-4815 TTY
ተጠርጣሪ የልጅ ጥቃትን ወይም ቸልተኝነትን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት ክፍል ለማሳወቅ 24/7 ሪፖርት የሚቀበል የስልክ መስመር።

ለአደጋ ተጋላጭ ጎልማሶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎት . . . . . . 240-777-3000፣ 240-777-4815 TTY
በአዋቂዎች ላይ የሚጠረጠር ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 ክፍት የሆነ የስልክ መስመር።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ መምርያ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል (24 ሰዓት) ስልክ፡- . . . . . . . . . . . . 240-773-5400
በልጆችና በጎልማሶች ላይ የሚፈጸሙ የወሲብ ወንጀሎችን፣ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን፣ ሸሽተው፣ የጠፉ ልጆች፣ ከባድ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የተጋላጭ አረጋውያን ጥቃት/አደጋ በአዋቂዎች ላይ የሚደርስ በደል፣ እና የተመዘገበ ሪከርድ ያላቸው የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ ለማሳወቅ 24/7 የስልክ መስመር።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ፡-**
የአደንዛዥ ዕፅ እና የወሮበሎች (ጋንግ) የጥቆማ መስመር። 240-773-GANG (4264) ወይም . . . . . . . . . . . . . 240-773-DRUG (3784)
በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ህገ-ወጥ እጽ ማዘዋወር/የወሮበሎች ቡድን (ጋንግ) እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት ማንነት ሳይገለጽ ጥቆማ ለማቅረብ 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

## MCPS ሪሶርሶች

ካውንቲ አቀፍ የተማሪ አመራር
www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership

ዳይሬክተር፣ የተማሪ አመራር ተግባራት. . . . . . . 240-740-3977

ተማሪ የቦርድ አባል
www.montgomeryschoolsmd.org/boe/members/student.aspx

የትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ስልክ፡- . . . . . . . . . 240-740-3030

የትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ ክፍል ዋና ኃላፊ . 240-740-3100

የልዩ አገልግሎት ድጋፍ ክፍል . . . . . . . . . 240-740-5630

ሰክሽን 504 አስተባባሪ . . . . . . . . . . . . 240-987-8031

## የሞንትጎመሪ ድንገተኛ ያልሆነ ሪሶርሶች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ

ድንገተኛ ላልሆነ ጉዳይ የስልክ መስመር. . . . . . . 301-279-8000

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች የመረጃ መስመር
የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ
አጠቃላይ መረጃን ያነጋግሩ . . . . . . . . 311, 301-251-4850 TTY
ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች . . . . . . . . . . . . . -777-0311

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች

በዚህ ድረ-ገጽ አማካይነት ከ MCPS ጋር ሁልጊዜ መገናኘት ይችላሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org

**አጠቃላይ ተቋሙን የሚመለከት መረጃና የአስቸኳይ ሁኔታ ማስታወቂያዎችን ለማግኘት፡-**

ትዊተር፡- MCPS on Twitter. . . . . . . . . . www.twitter.com/mcps

ትዊተር በስፓንሽኛ፡- MCPS en Español . . www.twitter.com/mcpsespanol

MCPS ፌስቡክ፡- . . . . . . . . . . . . . www.facebook.com/mcpsmd

ፌስቡክ በስፓንሽኛ፡- MCPS en Español . www.facebook.com/mcpsespanol

የማንቂያ/የማስጠንቀቂያ መልክቶች፡-
Alert MCPS . . . . . . . www.montgomeryschoolsmd.org/alertMCPS

988 SUICIDE & CRISIS LIFELINE

988 LÍNEA DE PREVENCIÓN DEL SUICIDIO Y CRISIS

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ክስተት ማስታወቂያዎች (የቀጠለ)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ፈጣን መልክቶች፣ የኢሜይል መልክቶች እና ዘገባዎች
MCPS QuickNotes Email Messages and Newsletter . www.mcpsQuickNotes.org

MCPS የመረጃ አገልግሎትን ይጠይቁ፡-
ስልክ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 240-740-3000
የስፓንሽኛ አስቸኳይ የስልክ መስመር 240-740-2845
Email . . . . . . . . . . . . . . AskMCPS@mcpsmd.org

MCPS የማህበረሰብ መረጃ ቢሮ 240-740-2837
MCPS Television www.mcpsTV.org;
ቴሌቪዥን

Comcast 34, 998; RCN 89, 1058; Verizon 36

በድምፅ የተቀረጸ የአስቸኳይ ጊዜ እና የአየር ሁኔታ መረጃ . . 301-279-3673

## MCPS ሪሶርሶች የሚገኙበት ድረ-ገጽ
www.montgomeryschoolsmd.org

ዳሰሳ ወይም ቅኝት፡-

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤቶች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

MCPS ስልታዊ (ስትራቴጂያዊ) እቅድ

አትሌቲክስ

Be Well 365

የትምህርት ቦርድ

ጉልበተኝነት፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ዛቻ/ማስፈራራት

የአውቶቡስ መስመሮች

የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት

የኮሌጅ እና የሙያ ማዕከል

የግንዛቤ ትምህርት Common Sense Education

የኮርስ ጥንቅር መግለጫ

የማህበራዊ ሚዲያዎችንና ሌሎች የዲጅታል መሳሪያዎችን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀምና የኢንተርኔት ደህንነት - Cybercivility and CyberSafety

የዲፕሎማ መስፈርቶች

ወሮበሎች (ጋንግ) እና የወሮበሎች ተግባር

## MCPS የሪሶርስ ድረ-ገጽ (የቀጠለ)
www.montgomeryschoolsmd.org

የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

የሃይማኖት ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች

ስለ ተማሪ ጾታዊ ማንነት መመሪያ

የምሣ ምግብ ዝርዝር

የሜሪላንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ምዘናዎች

ፀረ-መድሎአዊነት

በኦንላይን የመመረቂያ ትምህርት

የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት

መርኆች እና ደንቦች

የስነልቦና አገልግሎቶች

የተማሪ ሠራተኛ አገልግሎቶች

የልጅ መበደል እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማደረግ

ፍትኃዊ ተሐድሶ

በት/ቤት የካውንስሊንግ እገልግሎቶች

የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች

የትምህርት ቤት ደህንነት

ፆታዊ ጥቃት

የማህበራዊ ሚድያ ዲጂታል ሲትዝንሽፕ (Social Media Digital Citizenship)

ልዩ ትምህርት

ልዩ ፕሮግራሞች

ስልታዊ የእቅድ ዝግጅት

የተማሪ ስነ-ምግባር ደንብ

የተማሪ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መማር - eLearning

የተማሪ ግላዊ ጉዳይ

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት

ራስን መግደል መከላከል

የሰመር ትምህርት ቤት Summer School

# መግቢያ

የተማሪ የስነምግባር ደንብ ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች፣ እና ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስርአት ያለው እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢን ለመፍጠር የሚተገበር መመሪያ ነው። ስለሚጠበቅ ባህሪ፣ ደህንነት፣ እና ጣልቃገብነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች አዲስ ፖሊሲ አይፈጠርም፣ ነገር ግን የሜሪላንድ ህግ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች፣ እና የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች (ከዚህ በኋላ "ደንቦች") ተፈጻሚ ይደረጋሉ። የተማሪ የስነምግባር ህግ/ኮድ ተማሪዎች ህጎችን ሲጥሱ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ እና ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው የማስፈፀሚያ መመሪያ ነው። ስለ ቦርድ ፖሊሲዎች እና MCPS ደንቦችን በአጭሩ ያብራራል፣ ነገር ግን ማንኛውም ሰው MCPS ድረ ገጽ ላይ ባለው የፖሊሲዎች እና ደንቦች መመሪያ ውስጥ ሙሉውን የቦርድ ፖሊሲዎች እና የሞንትጎምሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችን ማግኘት ይችላል። ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች በጣም የሚያስፈልጓቸውን መመሪያዎች እና ደንቦች አጭር መግለጫ ለማግኘት፡- እባክዎ MCPS የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች መመሪያተ ጓዳኝ ሰነድ ይመልከቱ።

### ማጠቃለያ እና የአፈጻጸም መመሪያ




የተማሪ የስነምግባር ህግ ተማሪዎች MCPS ንብረት ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል፣ ይህም የትኛውንም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤት ወይም ሌላ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት/ፋሲሊቲ፣ MCPS በባለቤትነት የሚያ ስተዳድራቸውን ቦታዎችን ጨምሮ፤ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውቶ ቡሶች እና ሌሎች MCPS በባለቤትነት የያዛቸው፣ የሚያስተዳድራቸው ወይም የሚቆጣጠራቸው ተሽከርካሪዎች፣ እና ንብረቶች/ፋሲሊቲዎች እና/ወይም MCPS የሚደግፋቸው ተማሪዎች የሚሳ ተፉባቸውና የተለያዩ አክቲቪቲዎች የሚከናወንባቸው (ማለትም፡- የመስክ ጉዞዎች፣ ፕሮምዎች፣ ወይም የአትሌቲክስ ውድድሮች)ሁሉ ይመለከታል። ርእሰመምህሩ በምክንያታዊነት ጥፋቱ የተማ ሪዎችን ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኞችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል ብሎ ካመነ ወይም የስነ ምግባር ጥፋቱ ከተፈጠረ ወይም ምክንያታዊ በሆነ መልኩ በትምህርት ቤት እንቅስ ቃሴዎች ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ወይም ጣልቃገብነት ይፈጥራል ተብሎ ከተገመተ ከትምህርት ሰአት ውጭ እና ከትምህርት ቤት ንብረት ርቆ የሚፈፀም የተማሪ ጥፋት የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰዳል።

የተማሪ የስነምግባር ህግ የመጀመሪያው ክፍል በስቴት እና በፌደራል የስነስርዓት/የዲስፕሊን ፖሊሲዎች ላይ የተመሰረተ የቦርዱ የስነምግባር እና የደህንነት ፍልስፍና መገለጫ ነው። የተማሪ የስነምግባር ህግ ሁለተኛው ክፍል MSDE የስነምግባር ደንቦችን የሚዘረዝር እና ለእያንዳንዳቸው ምላሽ ሊሆኑ የሚችሉ የባህሪ ጣልቃገብነቶችን የሚጠቁም ሠንጠረዥ ነው። የባህሪ ጣልቃገብነት ሜትሪክስ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ገጽ 7 ላይ ይጀምራል። በተደጋጋሚ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልሶች ከገጽ 6 ጀምሮ ቀርበዋል። አባሪ ሰነዶቹ ተጨማሪ ደጋፊ መረጃዎችን ይሰጣሉ።

## የመጀመሪያ ክፍል I:- ስለ ባህሪ እና ደህንነት ፍልስፍና

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ጣልቃገብነት፣ ደህንነት፣ እና ስለ ደህንነት እቅድ፣ ቦርዱ ለሥርዓት እና ለአስተማማኝ የትምህርት አካባቢዎች የሚጠብቀውን፣ ለማስ ተማር እና ለመማር የወሰኑትን ያስቀምጣል - MCPS ትምህርት ቤቶች ለውጤታማ ትምህርት አስፈላጊ የሆኑ አወንታዊ፣ መከባበር የሠፈነባቸው፣ ሥነ-ሥርዓት እና ደህንነታቸው የተጠበቀ የትም ህርት አካባቢዎች ይሆናሉ። የተማሪዎችን ተሳትፎ ማዳበር፣ የተማሪዎችን ስኬት ማሳደግ፣ እና በተቻለ መጠን ከመከሰቱ በፊት የተማሪዎችን እኩይ ተግባር የሚከላከሉ አወንታዊ የት/ቤት ባህሎችን እና የት/ቤት ዳባብ ሁኔታዎችን የማሳደግ መርኅ ይከተላል።

ቦርዱ ሁሉም ሰው - ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ሰራተኞች—ሲተባበሩ፣ ዋጋ ሲሰጡ፣ እና እያንዳንዳቸው ሚናዎቻቸውን ሲያከብሩ MCPS ከሁሉም የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ስኬታማ የመማሪያ ሥፍራ እንደሚሆን ያምናል፤ ይህ ሊሆን የሚችለው ሁሉም መከባበር የሰፈነባ ቸውን ሥርዓታማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ አካባቢዎችን ለመጠበቅ፣ በመማር እና በማስ ተማር ላይ ያተኮሩ የጋራ አስተሳሰብ ያላቸው የባህሪ ተግባራት ጥቅም ላይ ሲውሉ ነው። ይህንን ለማሟላት የሚመለከታቸውና የሚከተሉት ሰዎች ሁሉም የድርሻቸውን እንዲወጡ ይጠይቃል።

- ተማሪዎች ለትምህርታቸው፣ ለግል ባህሪያቸው፣ እና ስለ መብቶቻቸው አጠቃቀም በሚመለከት ጉልህ ሃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች በትምህርት ማህበረሰብ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ፣ ድርጊታቸው የሚያስከትለውን የተጠያቂነት ውጤት እንዲቀበሉ፣ እና ለቦርዱ ፖሊሲዎች እና የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህጎች እና መመሪያዎች ተገዢ እንዲሆኑ ይጠበቃል።
- ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸው በሚጋጥሟቸው የባህሪ ስጋቶች፣ ልጆቻቸው በሚወስዷቸው እርምጃዎች ጭምር የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመወሰድ ከሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ጋር በትብብር መስራት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ማለት፡- በትምህርት ቤት ውስጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸው በተገቢው መንገድ እንዲመሩ ያበረታታሉ፣ እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ልክ እንደ ተማሪዎቻቸው ሁሉ በመሳተፍ እና ገንቢ በሆነ መልኩ በመተባበር አወንታዊ፣ ምቹ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ እና ለሁሉም ተማሪዎች ለመማር እና ለማስተማር ምቹ የሆነ የት/ቤት አከባቢዎችን ለመፍጠር አመቺ ይሆናል ማለት ነው።
- የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የሚጠበቅባቸውን አወንታዊ ባህሪ መጠበቅ አለባቸው፤ እንዲሁም ለተግባራዊ የትምህርት አሰጣጥ አስፈላጊ ሆነው መከባበር የሠፈነበት አካባቢ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል። ሰራተኞች የተማሪን ባህሪ ለመምራት እና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ለመጠበቅ ተገቢውን የአዎንታዊ ባህሪ-የጣልቃ ገብነት ስልቶችን እና ድጋፎችን መጠቀም አለባቸው።
- አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ሰራተኞቹ የተማሪ ባህሪ በትምህርት አካባቢው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚያሳድርበት ጊዜ ወይም የትምህርት አካባቢን ደህንነት ሥነ ሥርዓት በሚጥስበት ጊዜ ተመጣጣኝ የሆነ፣ ከትምህርት አሰጣጥ ጋር የሚስማማ፣ ወጥነት ያለው፣ እና በፍትሃዊነት የሚተገበሩ እርምጃዎችን ከቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድሎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት የሠፈነበት ፖሊሲ ጋር በማጣጣም ጣልቃ መግባት አለባቸው።
- የሜሪላንድ ህግ MCPS ተማሪዎች ከስህተታቸው እንዲማሩ እድል የሚሰጥ፣ በባህሪያቸው የሚደርስባቸውን ጉዳት እንዲያርሙ እና በባህሪያቸው ምክንያት የተበላሹ ግንኙነቶችን ወደነበረበት እንዲመለሱ የሚያደርግ ግንኙነትን የማሻሻል የስነስርዓት ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል። ይህ ማለት፡-
  - » የማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ ዋና ዓላማ በተሐድሶ ፣በማገገሚያነት እና ትምህርታዊ በሆኑ ስልቶችና፣
  - » ዘዴዎች በዋነኝነት አስቀድሞ በመንቃት እና በመከላከል ላይ ያተኮሩ ይሆናሉ፣
  - » ግንኙነቶችን ለማዳበር እና የሚጠበቅባቸውን ባህርይ በማደስ ላይ አጽንዖት ይሰጣል፣ እና
  - » ለደረሱ ጉዳቶች ምላሽ የመስጠት ተጠያቂነት ይኖራል።
- በስቴት ህግ እና MSDE መመሪያዎች ድንጋጌ መሰረት፣ MCPS --- መተግበሩን ይቀጥራል -
  - » ቀጣይነት ያለው የባህሪ ማስተካከያ ጣልቃገብነት፣ ---አጠቃቀምን ጨምሮ
  - » ለመማር ምቹ እና የአካዳሚክ ስኬትን የሚደግፍ አወንታዊ አካባቢን ለመጠበቅ የተነደፉ ተገቢ የሆነ ማባባስን የማስወገድ ስልቶች እና ቴክኒኮችን፣
- ከስቴት ህግ ጋር በማሟለጥ ከትምህርት ክፍል ማስወጣት፣ ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ማገድ፣ እና ማባረር እንደ የመጨረሻ አማራጭ ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል።

በቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ እንደተገለጸው፣ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት፣ አድሎአዊነትን አይታገስም። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የሁሉንም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ኃላፊነቶችን የመወጣት እና የማህበረሰባችንን የረዥም ጊዜ ጥረት ለማሳካት ፍትሃዊነትን፣ አካታችነትን፣ እና ሁሉንም ሰው የማካተት ብቃትን ያሰናክላል።

## ክፍል II፡- ባህርይ የማስተካከል ጣልቃገብነት ሜትሪክስ

MCPS ተገቢ ባህሪን መማር ለህጻናት የእድገት ሂደት መሠረታዊ መሆኑን ያምናል፤ የተማሪዎችን የተለያየ ባህሪ እና የእድገት ፍላጎቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ደረጃ በደረጃ የማስተካከያ ምላሽ ጣልቃገብነት የሚያሟሉ ስልቶችን የሚጠይቅ መሆኑ ይታመናል። ስለ መማሪያ ክፍል ጣልቃገብ ነቶች፡-(ደረጃ 1-2)፣ ዋና ጣልቃገብነቶች (ደረጃ 3-4) እና የሱፐርኢንተንደንት ጣልቃገብነቶች( ደረጃ 5) ማብራሪያ ለማግኘት ከገጽ 7–8 ይመልከቱ። በሚቀጥሉት ገፆች ላይ በሰንጠረዥ የተገ ለጹት የባህሪ ማስተካከያ ጣልቃገብነት ደረጃዎች በሚከተለው መልኩ መተግበር አለባቸው።



- የተዘረዘሩት የህግ ጥሰቶች በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) የተማሪ ሪኮርዶች መመሪያ ላይ ከተቀመጡት የዲሲፕሊን ኮዶች ጋር በቀጥታ ይገናኛሉ። ስለ እያንዳንዱ የህግ ጥሰት የተቀመጡት መግለጫዎች የተሟሉ አይደሉም።
- የባህሪ ማስተካከያ ምላሾች ከተማሪ እድገት እና ከእድሜ ጋር የተመጣጠኑ መሆን አለባቸው፤ እና በመጥፎ ባህሪ ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች በመደበኛነት፣ በፍትሃዊነት እና ለሁሉም ተማሪዎች የግል ትምህርታዊ እድገት እና የመማር እድሎችን በሚደግፍ መንገድ መተግበር አለባቸው።
- ሰራተኞች ---ጥረት ማድረግ አለባቸው-
  - » ተማሪዎችን በመቅጣት ረገድ ያለውን አድሎአዊነት እና ተመጣጣኝ አለመሆንን ማወቅ እና ማስወገድ እንዲሁም  የዲሲፕሊን ህጎችን ወጥነት ባለው መልኩ፣ በፍትሃዊነት ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል፤
  - » እያንዳንዱ ሰው ዋጋ ያለው የማህበረሰቡ አባል መሆኑን ማሳየት፣ ለተፈጠረበት እና ለማህበረሰቡ አወንታዊ አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ የታመነ፣ እና
  - » እንደ መጨረሻ አማራጭ ብቻ ተማሪዎችን ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት[1] እና በተቻለ ፍጥነት ተማሪዎችን ወደ ክፍል እንዲመለሱ ማድረግ፣
- ተገቢ ያልሆነ ወይም የመረበሽ ባህሪ የመጀመርያ ሲሆን፣ የት/ቤት ሰራተኛ መጀመርያ ማገናዘብ ያለበት ከሜትሪክሱ (Matrix) ውስጥ ከሁሉም አነስተኛውን የማስተካከያ ደረጃዎች ወይም የዲሲፕሊን ምላሾች መካከል (አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ማስተካከያዎች ወይም የዲሲፕሊን እርምጃዎች ከዝቅተኛ ደረጃ መጀመር) አለባቸው። ነገር ግን፣ አንዳንድ ጊዜ ሁኔታዎች የሚከሰቱት የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለአንድ ከባድ የሆነ የባህሪ ግድፈት በመጀመሪያ ደረጃም ቢሆን ከፍ ያለ የማስተካከል/የመከላከል ምላሽ እንዲሰጡ የሚያስገድድ ሊሆን ይችላል። (በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ገጽ 6 ይመልከቱ)

[1]የሜሪላንድ ህግጋት "Code of Maryland Regulations 13A.08.01.11(A)"(6)

## ችግርን የመፍታት፣የማቅለል መስፈርቶች

የባህሪይ ማስተካከል ጣልቃገብነቶች ከክስተቱ ጋር በተያያዙ አጠቃላይ ሁኔታዎች ላይ ተመስርተው መገምገም አለባቸው –

- የተማሪው(ዋ) ዕድሜ፣
- ባህሪው በሌሎች ላይ ስላሳደረው ተጽእኖ እና የተማሪው(ዋ) የግንዛቤ እድገት ደረጃ፣
- ቀደም ብሎ ያልታወቁ የትምህርት ፍላጎቶች ወይም ሁኔታዎች በተማሪው(ዋ) ህይወት ውስጥ ለሥነ ምግባር ጉድለት አስተዋፅዖ ያደርጉ እንደሆነ፣ እና
- የተማሪው(ዋ)ን ባህሪ ለመረዳት አውድ ሊፈጥሩ የሚችሉ ባህላዊ ወይም የቋንቋ ምክንያቶች

## የመባባስ መስፈርቶች

ርእሰ መምህራን ከዚህ በታች ያሉትን መመዘኛዎች ካገናዘቡ በኋላ ከፍ ባለ የጣልቃ ገብነት ደረጃ ምላሽ የመስጠት ውሳኔ ማድረግ ይችላሉ።

- ቀደም ሲል የተፈጸመው የስነ ምግባር ጉድለት፣ የበፊት የጥፋት ድርጊቶች ብዛት፣ እና ለእንደዚህ አይነት ጥፋቶች የተወሰዱ እርምጃዎች ወይም ውጤታማ አይደሉም ተብለው የተገመቱ የዲሲፕሊን እርምጃዎች
- በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት የማድረስ ዛቻ
- ከሌላ ጥፋት ጋር በጥምረት የተከሰቱ እኩይ ተግባራት
- የትምህርት ሂደትን/አሠራሮችን የሚያደናቅፍበት ሁኔታ
- በባህሪው ምክንያት የደረሰ ወይም የሚደርስ ጉዳት
- አፀያፊ ቋንቋን መጠቀም ወይም ጥላቻን የሚያበረታቱ ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን ማሳየት/ማሰራጨት

# በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

**የእኔ ተማሪ እርዳታ ማግኘት የሚችለው/የምትችለው ከየት ነው?**

ጉዳት የደረሰባቸው፣ በሌሎችን ላይ ጉዳት ያደረሱ፣ ወይም ጉዳት ሲደርስ የተመለከቱ ተማሪዎች ድጋፍ እና እርዳታ ለማግኘት የትምህርት ቤቱን አስተዳዳሪ ወይም ካውንስለር መጠየቅ ይችላሉ። MCPS ውስጥ እና ውጭ ድጋፍ ለማግኘት የሚችሉባቸውን ምንጮች ለማወቅ እባክዎ በዚህፈጣን የማጣቀሻ መመሪያ ፊት ገጽ ላይ ያለውንየተማሪ የስነምግባር ህግ ይመልከቱ።

**ርእሰ መምህሩ ወይም መምህሩ በሜትሪክሱ ላይ ከተገለፀው ያነሰ የጣልቃ ገብነት ደረጃ መጠቀም ይችላሉ?**

አዎ፣ የዲስፕሊን እርምጃን የማቅለል ሁኔታ የህግ ጥሰቱን ክብደት እና እንዲሁም የምላሹን ደረጃ በማገናዘብ ሊቀንሱ ይችላሉ። የማቅለል መስፈርቶች የሚከተሉትን ማገናዘብ አለባቸው፡-

- የተማሪው(ዋ) ዕድሜ፣
- ባህሪያቸው በሌሎች ላይ ስላለው ተጽእኖ እና የተማሪው(ዋ) የግንዛቤ እድገት ደረጃ፣
- በተማሪው(ዋ) ህይወት በግልጽ ያልታወቁ የትምህርት ፍላጎቶች ወይም ሁኔታዎች ለሥነ ምግባር ጉድለት አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ከሆነ፣ እና/ወይም
- ስለ ተማሪው(ዋ) ባህሪ ለመረዳት አውድ ሊሰጡ የሚችሉ ባህላዊ ወይም የቋንቋ ምክንያቶች ካሉ።

የባህሪ ጣልቃገብነት አላማ የተጎዱትን ግለሰቦች ለመደገፍ ሲሆን በሌሎች ላይ ጉዳት ያደረሱ ተማሪዎች ለድርጊታቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ እና ያደረጉትን ጉዳት እንዲገነዘቡ እና እንዲረዱ፣ እና የሚማሩትን ማህበረሰብ ለመፍጠር እና ለመንከባከብ አወንታዊ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ማበረታታት ነው። ተማሪዎች ከስህተታቸው እንዲማሩ እድል ይሰጣቸዋል።

**ርእሰ መምህሩ እርምት ለመውሰድ ከፍ ያለ የጣልቃገብነት ደረጃ መጠቀም የሚችለው መቼ ነው?**

የሚያባብሱ ሁኔታዎች ስህተትን ወይም ጥፋትን ሊያቀጣጥሉ ወይም የበለጠ ከባድ ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ስለዚህ ከፍ ያለ ምላሽ ሊተገበር ይችላል። በሜሪላንድ ህግ የሚጠበቀው የባህሪ ጣልቃገብነት ተማሪዎችን በትምህርት ክፍል ውስጥ ማቆየት እና ከትምህርት ቤት እና ከመደበኛ የትምህርት መርሃ ግብራቸው ጋር እንዲቆራኙ ቢሆንም፣ በሜሪላንድ ህግ መሠረት ርእሰ መምህራን የዲስፕሊን ርምጃን/ተግሣጽን የመወሰን ኃላፊነት እንዳላቸው ይገልጻል። ርእሰ መምህራን ከዚህ በታች ያሉትን የሚያባብሱ ሁኔታዎችን ካገናዘቡ በኋላ ከፍ ባለ የጣልቃ ገብነት ደረጃ ምላሽ የመስጠት ውሳኔ መስጠት አለባቸው።

- ቀደም ሲል የተፈፀመ የሥነ ምግባር ጉድለት፣ በፊት የተፈፀሙ የሥነ ምግባር ጉድለቶች ብዛት፣እና ደካማና  ውጤታማ አይደሉም ተብለው የተገመቱ የተወሰዱት የእርምት ዲሲፕሊን እርምጃዎች፣
- በሌሎች ተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት የማድረስ ዛቻና ሥጋት
- ከሌላ ጥፋት ጋር በጥምረት የሚከሰቱ እኩይ ተግባራት
- የትምህርት ሂደትን/አሠራሮችን ማደናቀፍ
- በባህይ ምክንያት የሚደርስ ጉዳት
- ቋንቋን መጠቀም ወይም ጥላቻን የሚያበረታቱ ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን ማሳየት/መለጠፍ/መጻፍ

ርእሰ መምህራን በሜትሪክሱ ላይ ከፍተኛው ደረጃ በላይ ወይም ከተገለጸው ዝቅተኛ ደረጃ በታች ምላሽ ለመስጠት እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት በትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ ክፍል (DLSI) ከአካባቢ ያቸው ተባባሪ ሱፐርኢንቴንደንት ጋር መማከር አለባቸው። ምላሹን ወደ መታገድ ወይም መባረር ደረጃ ማድረስ አስፈላጊ ከሆነ ገጽ 6 ይመልከቱ።

ቦርዱ ቋንቋን በመጠቀም ወይም ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን በማሳየት፣ በመለጠፍ ጥላቻን የሚያ በረታቱ ድርጊቶችን የዲሲፕሊን ምላሽ ደረጃን ከፍ የሚያደርግ፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈ ራራት፣ ወይም ንብረት ማውደም፣ ወይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ስራዎች ወይም እንቅስ ቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ረብሻ ይፈጥራል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ እንደ በቂ ምክንያት ሊወሰድ እንደሚችል መመሪያ ሰጥቷል። እነዚህ ማመሳከሪያዎች የሚያካትቱት ቋንቋን/ቃላትን በመጠቀም ወይም እና/ወይም የዘር መድልዎን የሚያበረታቱ ምልክቶችን እና ምስሎችን መለጠፍ፣ግላዊ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ የዘረ ኝነት ስድብን ጨምሮ መድልዎ የሌለበት፣ ፍትሃዊነት እና የብቃት ባህል የሠፈነበት በቦርድ ፖሊሲ ACA ውስጥ የተገለጹትን ድንጋጌዎች የሚጥሱ ተግባሮችን ሊያካትቱ ይችላሉ።



| ሠንጠረዥ 1፡ ከሜትሪክሱ ላይ በተግባር የሚውሉ የባህሪ ማሻሻያ ጣልቃገብነት ደረጃዎች | |
|---|---|
| ደረጃ 1 | **በክፍል- ውስጥ በአስተማሪ የሚወሰድ እርምጃ**<br>መምህራን በክፍል ውስጥ እና በተማሪ መደበኛ የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ ተገቢውን ባህሪ ለማስተማር እና ለማጠ ናከር የማስተማሪያ ቴክኒኮችን እና የባህርይ አያያዝ ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዲማሩ እና ለአስተማማኝ የትምህርት አካባቢ አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ፣ በእውቀት እንዲበለጽጉ፣ እና ለተማሪ ማህበረሰቡ ተጠያቂ መሆን እንዳለባቸው በሚወ ስዱት የስነምግባር እርምጃ ያበረታታሉ። ተስማሚ የሆኑ ስልቶች የተማሪን እድሜ እና የዕድገት ደረጃ ያካትታሉ፡-<br>• የተሐድሶ ተግባሮች (በክፍል ውስጥ)<br>• የቃል እርማት፣ ማሳሰቢያ/አቅጣጫ ማመላከት፣ በጽሁፍ መግለጽ/ይቅርታ እንዲጠየቅ ማድረግ፣ ሚና መጫወት፣ የዕለት ተዕለት የሂደት ማስታወሻ<br>• ማገድ<br>• እንደአስፈላጊነቱ ከወላጅ/ከአሳዳጊ ጋር ለመወያየት (ወላጅን/አሳዳጊን በስልክ፣ በኢሜል ወይም በጽሑፍ መጥራት) -<br>» ተማሪው(ዋ) ከትምህርት ቀናት ውጪ የሚያደርጋቸው/የምታደርጋቸው ምግባሮች ክፍል ውስጥ ከሚታዩበ(ባ)ት ባህርያት ጋር ተዛማጅነት ሊኖረው ይችላል።<br>» እስካሁን የተተገበሩ እና ወደፊትም የሚቀጥሉ ስልቶች<br>» በትምህርት ቤት መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ እና/ወይም በመከላከል ላይ ያተኮረ ምክር መለገስ፣<br>» በትምህርት ቤት የግጭት አፈታት ዘዴ<br>• ወደ ካውንስለር ወይም የተማሪ ደህንነት ቡድን ማስተላለፍ |
| ደረጃ 2 | **በክፍል ውስጥ - በመምህር የሚሰጥ የምክክር እና የድጋፍ መርጃዎች**<br>በክፍል ውስጥ እና በተማሪው መደበኛ የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ባህሪን ለማረም የማስተማሪያ ቴክኒ ኮችን እና የባህሪ አያያዝ ስልቶችን በማስተባበር መምህራን ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሌሎች ደጋፊ ሰራተኞችን ያሳትፉሉ ፣በሌሎች ላይ የደርሰውን ጉዳት በመጠገን፣ ለሚማሩ ማህበረሰቦች እና ለተማሪዎች ትምህርት ተጠያቂነት መኖሩን ማስረጽ ይገባል። ከድጋፍ ሰጪ ሪሶርሶችጋር በመመካከር፣ ሰራተኞች ችግር ያለባቸው ባህሪያት ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉ ነገሮችን የመቀነስ እርምጃዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ደረጃ 2 ላይ የሚወሰዱ የእርምጃ ስልቶች ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ይጨምራሉ፡-<br>• ሁሉንም የደረጃ 1 አማራጭ እርምጃዎች (በአስተማሪ ውሳኔ)<br>• የወላጅ/የአሳዳጊ እና የተማሪ ኮንፈረንስ (ከአስተማሪ እና/ወይም ከድጋፍ ሰራተኞች ጋር)<br>• የተሐድሶ እርምጃዎች (በትምህርት ክፍል ወይም በፍትሃዊ ተሃድሶ አሰልጣኝ፣ ስፔሻሊስት፣ ወይም ሌላ የድጋፍ ሰራተኛ አማካኝነት ተግባራዊ እንዲደረግ የተመቻቸ)<br>• የትምህርት አስተዳደር ቡድን ኮንሰልቴሽን<br>» ተግባራዊ የስነ ምግባር ግምገማ/የስነ ምግባር ማስተካከያ እቅድ<br>» የስነምግባር ስምምነት መፈረም<br>» የማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት<br>» ከትምህርት ቤት ካውንስለሮች/የሪሶርስ ስፔሻሊስቶች ጋር በተወሰነ እቅድ መገናኘት<br>» ወደ MCPS ወይም የማህበረሰብ ሪሶርሶች ማስተላለፍ |
| ደረጃ 3 | **በርእሰመምህር የሚወሰዱ እርምጃዎች**<br>ርእሰ መምህራን በሌሎች ወይም በተማሪ ማህበረሰብ እና በተማሪ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ስለመጠገን፣ ስለ ተማሪ ተጠያ ቂነት አፅንዖት ሰጥተው ለመነጋገር ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሌሎች ደጋፊ ሰራተኞችን ያሳትፋሉ። የባህሪ አያያዝ ስልቶች ተማሪን በመደበኛ የትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ ለማቆየት የሚደረግ ጥረት ቢሆንም፤ ነገር ግን የግዴታ ከሆነ ተማሪን ከክፍል ውስጥ ለአጭር ጊዜ ማስወገድ እና በተቻለ ፍጥነት ወደ መማሪያ ክፍል መመለስ ያስፈልጋል። ደረጃ 3 ላይ የሚወሰዱ ምላሾች ከሚከተሉት ስልቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ተግባራዊ ይደረጋሉ።<br>• ደረጃ 1 እና 2 አማራጮች በሙሉ (በርዕሰ መምህር ውሳኔ)<br>• ስለ ጉዳዩ ለመወያየት የወላጅ/የአሳዳጊ እና የተማሪ ኮንፈረንስ ማድረግ (ከርዕሰ መምህር ጋር) -<br>» ደረጃ 2 ላይ የተወያዩትን ማናቸውንም አማራጮች<br>» ከርዕሰ መምህር፣ ከትምህርት ቤት ካውንስለሮች፣ ወይም ከሪሶርስ ስፔሻሊስቶች ጋር በተወሰነ ጊዜ መገናኘት<br>» መምህር፣ ተማሪ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ኮንፈረንስ ማድረግ<br>• የተሐድሶ እርምጃዎች (በክፍል ውስጥ ወይም በፍትኃዊ ተሃድሶ አሰልጣኝ፣ ስፔሻሊስት ወይም ሌላ ደጋፊ ሰራተኛ አባል እንዲተገበር ማመቻቸት)<br>• መመለስ/መካስ<br>• ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ላይ ከመሳተፍ ለተወሰነ ጊዜ መገደብ/ማገድ<br>• ት/ቤት ጣልቃ ገብነት<br>• ት/ቤት እንዲታገድ/እንድትታገድ ማድረግ |

| ሠንጠረዥ 1፡ ከሜትሪክሱ ላይ በተግባር የሚውሉ የባህሪ ማሻሻያ ጣልቃገብነት ደረጃዎች | |
|---|---|
| ደረጃ 4 | **በርእሰመምህር የሚወሰድ እርምጃ**<br>ርእሰ መምህራን የተማሪ ተጠያቂነትን አስፈላጊነት አፅንዖት በመስጠት ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና ሌሎች ደጋፊ ሰራተኞችን በማሳተፍ ውይይት ማድረግ እና በሌሎች ላይ ወይም በተማሪ ማህበረሰብ እና በተማሪ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት እንዲጠገን ማድረግ። የባህሪ አያያዝ ስልቶች ትግበራ ላይ ተማሪን በመደበኛ አካዴሚያዊ ፕሮግራም ውስጥ ለማቆየት ጥረት ይደረጋል፤ ነገር ግን እንደ መጨረሻ አማራጭ ተማሪን ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ሊያስወግዱ እና[2] በተቻለ ፍጥነት ተማሪን ወደ ክፍል ትምህርት እንዲመለስ ማድረግ ይችላሉ። የደረጃ 4 ምላሾች እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ ከሚከተሉት ስልቶች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ይተገበራሉ።<br>• የደረጃ 1፣ 2፣ እና 3 አማራጮች በሙሉ (በርዕሰ መምህር ውሳኔ)<br>• የአጭር ጊዜ እገዳ (እስከ 3 ቀናት)<br>• የረጅም ጊዜ እገዳ (4-10 ቀናት) |
| ደረጃ 5 | **በሱፐርኢንተንደንት/በተወካይ የሚወሰዱ እርምጃዎች**<br>እነዚህ ምላሾች አንድን ተማሪ ከ 11 እስከ 44 ቀናት ከመደበኛ የትምህርት መርሃ ግብራቸው በተራዘመ እገዳ እንዲቆዩ ማድረግ አለበለዚያ 45 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ከት/ቤት መባረር ማለት ነው። (ደረጃ 5)<br>የተራዘመ የማገድ እርምጃ ለመውሰድ ወይም ለተራዘመ ጊዜ ከ ት/ቤት ለማባረር በሜሪላንድ ህግ የተገለጹትን የጥፋት መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-<br>• በሌሎች ተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማድረስ ዛቻና ሥጋት፣ ወይም<br>• ተማሪው(ዋ) በትምህርት ቀን ሌሎች ተማሪዎች በጥሞና መማር እንዳይችሉ ከፍተኛ እንቅፋት የፈጠረ እና በትምህርት ሂደት ላይ ሥር የሰደደ እና ከፍተኛ ረብሻ በመፍጠር የተሰማራ(ች) ከሆነ እና ቀደም ሲል ሌሎች ተገቢ የስነምግባር እና የዲሲፕሊን ጣልቃገብነት እርምጃዎች ተሞክረው ለውጥ ያላሳየ(ች) መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።<br>• ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ተማሪው(ዋ) ከትምህርት የሚገለልበትን/የምትገለልበትን ጊዜ በተቻለ መጠን በጣም አጭር ጊዜ እንዲሆን መወሰን አለበት፣ እና<br>• MCPS ከትምህርት ቤት ለተገለለ(ች)ው ተማሪ --- መስጠት አለበት።<br>» ተመጣጣኝ የትምህርት አገልግሎቶችን እና<br>» የተማሪው(ዋ)ን በተሳካ ሁኔታ ወደ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም እንደሚመለስ/እንደምትመለስ ለማረጋገጥ ተገቢ የባህሪ ድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት[3] |

### በአውቶቡስ ጉዞ ላይ የተማሪ የስነምግባር ህግ ተፈጻሚ ይደረጋል?

አዎ፣ የተማሪ የስነምግባር ህግ ተማሪዎች በማንኛውም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ በሚሆኑበት ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል፣ ይህም ማለት አውቶቡሶች እና ሌሎች MCPS በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው፣ ወይም ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ በኪራይ/በኮንትራት የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎችን ሁሉ ያካትታል።[4]

የተማሪ ስነምግባር መመሪያ እና/ወይም የአውቶቡስ ደህንነት ህጎችን የሚጥሱ ተማሪዎች የሚከተሉትን የአፈጻጸም ሂደቶች መሰረት በማድረግ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ውሳኔ የአውቶቡስ መጓጓዣ መብት ሊነፈጉ ይችላሉ፡ (1) የአውቶቡስ ኦፐሬተሩ(ሯ) የትምህርት ቤት አውቶቡስ የዲሲፕሊን ሪፖርት MCPS ቅጽ 555-3 በመሙላት ተማሪው(ዋ) በትምህርት ቤት አውቶቡስ ላይ የፈፀማቸውን የዲሲፕሊን ችግሮች የሚመለከቱ ዝርዝሮችን ለርዕሰ መምህር ያሳውቃል። (2) በትምህርት ቤቱ የተወሰደው እርምጃ የዲሲፕሊን ችግሮቹን ካልፈታ ኦፐሬተሩ ለተጨማሪ እርምጃ MCPS የትራንስፖርት መምሪያ ክላስተር ተቆጣጣሪን ያነጋግራል።

### ተማሪ ከትምህርት ቤት ውጭ ለሚያደርገው የስነምግባር ጉድለት የዲስፕሊን እርምጃ ሊወሰድበ(ባ)ት ይችላል?

አዎን። ከ MCPS ንብረት ውጭ የሚፈፀም የተማሪ ጥፋት ከት/ቤት መቼት ጋር ግንኙነት ካለው፣ የትምህርት አካባቢው በአካልም ሆነ ቨርቹዋል ቢሆንም፤ ምግባሩ የሌሎችን ተማሪዎች ትምህርት የመጉዳት አደጋ የሚፈጥር ከሆነ፣ ወይም ድርጊቱ የትምህርት ሥራን የሚያደናቅፍ ከሆነ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

### አንድ ተማሪ ከክፍል ሊባረር የሚችለው መቼ ነው?

ተማሪዎችን ከትምህርት ክፍል ውስጥ ማስወጣት እንደ መጨረሻ አማራጭ ብቻ ተግባራዊ መሆን አለበት፤ ቢሆንም ግን ተማሪዎች በተቻለ ፍጥነት ወደ መማሪያ ክፍል መመለስ አለባቸው ተብሎ ይጠበቃል። "ማስወገድ" ማለት ተማሪ እራሱን እንዲቆጣጠር፣ ገለል እንዲል፣ ወደ ርእሰ መምህር ቢሮ እንዲሄድ ወይም የበለጠ ከባድ የዲስፕሊን እርምጃ የሚወሰድበት ጊዜ ማለት ነው። እባክዎን "የማስወገድ" በሂደት እንዴት እንደሚስተካከል እና በማን እንደሚተገበር ሜትሪክሱን ይመልከቱ።

### ዕረፍት እንዳይወስድ/እንዳትወስድ ሊከለከል ይችላል?

ለምን እና በምን ያህል ተደጋጋሚ ጊዜ እንደሆነ  መታየት ይኖርበታል። MSDE የአካል ማጎልመሻ ትምህርት መመሪያ የትምህርት ቤት ሰራተኞች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እና የእረፍት ጊዜን በዲስፕሊን ቅጣት ምክንያት መከልከል እንደሌለባቸው ይደነግጋል፣ እንዲሁም ወጣት ተማሪዎች ለጨዋታ እና ለጠንካራ የአካል ብቃት እድገት እድል እንዳላቸው የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ያረጋግጣል። ነገር ግን፣ ርእሰ መምህሩ ልጅ በእረፍት ጊዜ በእራሱ ወይም በሌሎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በተመለከተ ምክንያታዊ የደህንነት ስጋቶችን ለመከላከል እርምጃ ከተወሰደ እንደ "ቅጣት" አይቆጠርም።

"ምክንያታዊ የደህንነት ስጋቶችን" የመከላከል እርምጃዎች የሚወሰኑት በርዕሰ መምህሩ ነው። የተማሪው ባህሪ የርእሰመምህሩን/የተወካዩን፣የካውንስለር፣የትምህርት ቤቱን የስነ-ልቦና ባለሙያ፣የተማሪ ሰራተኛን ወይም ሌላ ስፔሻሊስትን ትኩረት ሊጠይቅ ይችላል፣ስለሆነም እንዲህ አይነት ትኩረት መሰጠት ያለበት እርምጃ የሚወሰደው በእረፍት ጊዜም ጭምር ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ ከእረፍት፣ ከጨዋታ፣ እና ከአካል ብቃት እንቅስቃሴ የማግለል ዘይቤ ስለማይፈቀድ የታለመ የተማሪ የድጋፍ እርምጃ ግምት ውስጥ መግባት አለበት።

### ተማሪዎች በቡድን መቀጣት ይቻላሉ?

አይሆንም። በአንዳንድ የቡድን አባላት የሆኑ ተማሪዎች መጥፎ ድርጊት ምክንያት የተማሪዎች ቡድን በጅምላ የዲስፕሊን እርምጃ ሊወሰድባቸው አይችልም። ለምሳሌ፡- አንድ ተማሪ ክፍል ውስጥ ቢረብሽ/ብትረብሽ፣ በክፍል የሚገኙትን ተማሪዎች በጅምላ በጊዜያዊነትም ቢሆን ማገት አይቻልም። ለጥፋቱ ተጠያቂ መሆን ያለበት ሰው ባይታወቅም ይህ ህግ የፀና ይሆናል።

### አንድ ተማሪ ወይም የክፍል ተማሪዎች በሙሉ በቅጣት መልክ የአካዳሚክ ሥራ እንዲሠራ መጠየቅ ይቻላል?

አይሆንም። አስተማሪ ለመቅጣት ብቻ ተብሎ ስራ እንዲሠሩ መመደብ አይቻልም (ለምሳሌ፡- ተማሪውን ደጋግሞ እንዲጽፍ ወይም ከመዝገበ-ቃላት እንዲገለብጥ ማድረግ አይችልም)። ይሁን እንጂ አንድ ተማሪ ትምህርት ሊያገኝበት የሚችል ከሆነ ከሚወስደው ትምህርት ጋር የተያያዘ ጠቃሚ ነገር እንዲያስተምር ሊመደብ ይችላል። የተማሪው ድርጊት በሌላ ተማሪ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንዳሳደረ የሚገልጽ ጽሑፍ እንዲጽፍ ማድረግ ተቀባይነት ያለው የአካዳሚክ ተግባር ተምሳሌት ነው።

መቼም ቢሆን የትምህርት ውጤቶች የባህሪ ማስተካከያ አይደረጉም። ነገር ግን፣ ታማኝነት የጎደለው የአካዳሚክ ድርጊት መዘዝ (ለምሳሌ፡- የሌላ ሰው የአካደሚክ ሥራ ቀድቶ የራስ ሥራ አስመስሎ ማቅረብ፣ ወይም የአካዳሚክ ሪኮርዶችን መቀየር) MCPS ደንብ IKA-RA፣ ውጤት መስጠት እና ሪፖርት ማድረግ በሚለው ዝርዝር ውስጥ ተገልጿል።

### MCPS ተማሪን በአካል መቅጣት ይችላል?

አይቻልም። ተማሪ በፍፁም አካላዊ ቅጣት ሊፈፀበት አይችልም። ነገር ግን፣ በሜሪላንድ ህግ፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ግጭትን ለመበተን፣ ጥቃትን ለመከላከል፣ ወይም የሚረብሽ ተማሪን ለመግታት ምክንያታዊ የሆነ ሃይል ሊጠቀሙ ይችላሉ። MCPS ደንብ JGA-RA የተማሪ ባህሪ ማስተካከያ ጣልቃገብነት እና ደንብ COB-RA ሪፖርት ሊደረጉ የሚችሉ ክስተቶች ላይ ከተገለጹት የተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር አካላዊ እገዳን መጠቀም በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተከለከለ ነው።

### አንድ የመማሪያ ክፍል ወይም ትምህርት ቤት የራሳቸውን የሥነ ምግባር ደንቦች መፍጠር ይችላሉ?

አዎን። ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ክፍል የሥነ ምግባር ሕጎች ከሕግ፣ ከቦርድ ፖሊሲ፣ ከሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች ወይም ህጎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ለትምህርታቸው እና ለግል ምግባራቸው እንዴት ኃላፊነት እንደሚወስዱ ለማረጋገጥ የራሳቸውን የሥነ-ምግባር ደንብ እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

ለምሳሌ፡- የትምህርት ቤት ሰራተኞች ተማሪዎች የራሳቸውን እድሜ እና ለዕድገት ተስማሚ የሆነ ቋንቋ እንዲያመነጩ ለማበረታታት የሚከተለውን ዝርዝር ሊጠቀሙ ይችላሉ።

1. የኔ ቃላት፣ ተግባር፣ እና አቋም/አመለካከት በማንኛውም ጊዜ ለራሴና ለሌሎች ያለኝን ክብር ይገልፃሉ።
2. በሰዓቱ ወደ ት/ቤት በመምጣት/በወቅቱ በመድረስ፣ በስነስርአት በመልበስ፣ እና በትምህርቴ ለማተኮር ዝግጁ በመሆን በራሴ፣ በወደፊቴ እና በት/ቤቴ ያለኝን አክብሮት/ከበሬታ/ኩራት አሳያለሁ።
3. ግጭቶችን ለመፍታት ሁልጊዜ የምፈልገው ይበልጥ ሰላማዊ መንገዶችን ሲሆን፣ ግጭቶችን በገዛ ራሴ በሰላም ልፈታቸው ካልቻልኩ የመምህራንን፣ የአስተዳዳሪዎቼን፣ ወይም የት/ቤት ሰራተኞችን እርዳታ ማግኘት እፈልጋለሁ።
4. በሌሎች የት/ቤት ማህበረሰብ ላይ ያደረስኩትን የሆነ ጉዳት/በደል ለማረም ዝግጁ እሆናለሁ።
5. ሰላማዊ እና ንፁህ የመማርያ አካባቢ በት/ቤቴ በማራመድ ኩራት/ከበሬታ ይሰማኛል።

### ፍትሐዊ ተሃድሶ ምንድን ነው?

ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ ዋና አላማው ተሐድሶ፣ ማገገሚያ፣ እና ትምህርታዊ እንዲሆን የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል። ለድርጊቶቹ ተጠያቂነት እና የተሐድሶ ልምዶች ቁልፍ ናቸው፣ እና ፍትሃዊ ተሃድሶ በምንም መልኩ ለደህንነት ከሚደረግ ቁርጠኝነት ጋር አይቃረንም። የተማሪ የስነምግባር ህግ  የተማሪ ማህበረሰቦችን ተጠያቂነት እንዲኖር ማድረግ እና  አንድ ሰው ሲጎዳ ወደነበረበት ተሐድሶ እንዲመለስ ማድረግን ይመለከታል። ከገጽ 26–28 ያለውን የባህሪ ጣልቃገብነት ዝርዝር ይመልከቱ።

[2]የሜሪላንድ ህግጋት/Code of Maryland Regulations 13A.08.01.11(A)(6)

[3]የሜሪላንድ ህግጋት ኮድ/Code of Maryland Regulations 13A.08.01.11B(2)፤(3)

[4]MCPS ደንብ EEA-RA፣ ስለ ተማሪዎች መጓጓዣ/ትራንስፖርት

### MCPS ንብረት ላይ ወንጀል ተፈጽሞ ሪፖርት ሲደረግ ምን ይሆናል?

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ MCPS ንብረት ላይ ለሚገኙ ሰዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ ሰላማዊ ትምህርት ቤቶችን እና የስራ ቦታዎችን ለመፍጠር እና ተማሪዎች እና ሰራተኞች ምርጥ ስራቸውን የሚያከናውኑበት እና የሚበለጽጉበት ሥፍራ ለመስጠት ቁርጠኛ ነው። ስለሆነም MCPS ለፍትሃዊ ተሐድሶ ቁርጠኛ ነው፣ ከባህሪ ጣልቃገብነት/ከፍትሃዊ የማገገሚያ ሂደት በተለየ MCPS ከሞንትጎሞሪ ካውንቲ የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ጋር የወንጀል ድርጊቶችን የመከላከል ምላሽ ስለመስጠት የመግባቢያ ስምምነቶችን ይመሠርታል። (ለምሳሌ፡- ዝርፊያ፣ በቡድን የተቀናጁ ክስተቶች/ወንጀሎች፣ የጦር መሳሪያዎች፣ አስገዳጅ ወሲባዊ ድርጊቶች፣ ፈንጂዎች) ወይም ሌሎች ከባድ አደጋዎች የተማሪዎችን እና የሰራተኞችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ የቃጠሎ ማስፈራራት፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አደገኛ ንጥረ ነገሮች/የአደንዛዥ እፅ ስርጭት፣ ንብረት ማውደም የመሳሰሉትን ይመለከታል። (በተጨማሪም ደንብ COB-RA የአደጋ ክስተትን ሪፖርት ማድረግላይ MOU ትግበራ እና የህግ አስከባሪ አካላት MCPS ንብረት ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች እና ከባድ አደጋዎች ምላሽ የመስጠት ሚናን ይመልከቱ።)

### ተማሪ ሊታገድ ወይም ሊባረር የሚችለው መቼ ነው?

በሜሪላንድ ህግ መሠረት፥ “በትምህርት ቤት” እገዳ መወሰን (በአንድ የትምህርት አመት ከ10 ቀናት ያልበለጠ)፣ “ለአጭር ጊዜ” ከትምህርት ቤት ውጭ እገዳ መወሰን (እስከ 3 የትምህርት ቀናት) ወይም “ለረጅም ጊዜ” ከትምህርት ቤት ውጭ እገዳ መወሰን (4-10 የትምህርት ቀናት) በሜትሪክሱ ጣልቃገብነት ደረጃ 4 በተገለጸው መሠረት በርዕሰ መምህር ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

ከ11 እስከ 44 ቀናት የሚቆይ የተራዘመ ከትምህርት ቤት መታገድ ወይም ለ 45 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ ከትምህርት ቤት የማባረር ውሳኔ ለመስጠት በተማሪው(ዋ) የተፈፀሙት ጥፋቶች በሜሪላንድ ህግ የተገለጹትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው እና ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ በሚከተሉት ምክንያቶች ሲወስን ሊተገበር ይችላል፡-

1. በሌሎች ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማድረስ አደጋ/ስጋት ከተፈጠረ፣ ወይም
2. የተማሪው(ዋ) ድርጊት በትምህርት ቀን ውስጥ ለሌሎች ተማሪዎች ለመማር ከፍተኛ እንቅፋት የሚፈጥር ከሆነ፣ በትምህርት ሂደት ላይ ሥር የሰደደ እና ከፍተኛ መስተጓጎል የሚፈጥር ከሆነ፣ ከዚህ በፊት የተወሰዱት እርምጃዎች እና ሌሎች ተገቢ የስነምግባር እና የዲሲፕሊን ጣልቃገብነቶች ተገቢ ማሻሻል ያላሳዩ ከሆነ ነው።
3. ሱፐርኢንተንደንቱ/ተወካዩ ተማሪን ከት/ቤት የማግለል ጊዜ በተቻለ መጠን በጣም አጭር ጊዜ እንዲሆን መወሰን አለበት፣ እና
4. ተማሪው(ዋ)ን ወደ መደበኛ የትምህርት መርሃ ግብር በተሳካ ሁኔታ እንዲመለስ/እንድትመለስ ለማድረግ MCPS ለተገለለ(ች)ው ተማሪ ተመጣጣኝ ትምህርታዊ አገልግሎቶችን እና ተገቢ የስነምግባር ድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት አለበት።

በስቴት ህግ መሰረት በአጠቃላይ ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 2ኛ ክፍል ላሉ ህጻናት ከትምህርት እገዳ እና ማባረር በጣም ውስን በሆኑ ሁኔታዎች ብቻ ሊተገበሩ ይችላሉ። የሜሪላንድ ህግ ከቅድመ መዋእለ ህጻናት እስከ ሁለተኛ ክፍል (K-2) የተማሪዎችን ከት/ቤት መታገድ እና መባረር እንደሌለባቸው ከፍተኛ ገደቦችን አስቀምጧል። ርእሰ መምህራን/ተወካዮች ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ሠራተኞች በሌላ አይነት ማስተካከያ እና ድጋፍ በመስጠት ጉዳቱን ለመቀነስ ወይም ለመከላከል የማያስችል አይቀሬ ከባድ ጉዳት የሚያስከትል ዛቻ/ስጋት መኖሩን ለመወሰን የት/ቤት የስነልቦና ባለሙያ ወይም ሌላ የአእምሮ ጤና ባለሙያ ማማከር አለባቸው። የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር/ተወካይ እገዳ መወሰን ግዴታ ከሆነ፣ ከውሳኔው አስቀድሞ ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ DLSI የሚመለከተውን የትምህርት ስኬት እና አስተዳደር ዳይሬክተር ጋር መነጋገር አለባቸው። የእገዳ ጊዜ ርዝመት ከአምስት የትምህርት ቀናት መብለጥ የለበትም። በፌዴራል ህግ መሠረት ከቅድመ መዋእለ ህጻናት እስከ 2ኛ ክፍል ላሉ ህጻናት ከት/ቤት መባረር በውስን ሁኔታዎች ብቻ የተገደበ ነው። MCPS ደንብ JGA-RB ከት/ቤት መታገድ እና መባረር ይመልከቱ።

### ከት/ቤት የመታገድ ወይም የመባረር ውሳኔን ይግባኝ ማለት ይቻላል?

አዎ። ከት/ቤት የማገድ ወይም የመባረር ውሳኔ ይግባኝ ሊባል ይቻላል።

የአጭር ጊዜ ወይም የረጅም ጊዜ ከት/ቤት እገዳ (10 ቀናት ወይም ከዚያ ያነሰ)፡- ወላጅ/አሳዳጊ ልጃቸው 10 ቀናት ወይም ከዚያ ያነሰ ጊዜ ከት/ቤት ከታገደ(ች) ተጨማሪ መረጃዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል ብለው ካመኑ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ ርእሰመምህርን መጠየቅ ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ያንን መረጃ በኢሜል ወይም በደብዳቤ ወዲያውኑ ለርእሰመምህሩ መላክ አለባቸው። ርእሰ መምህሩ/መምህሩ ውሳኔያቸውን እንደገና ካላጤኑ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ባለው መረጃ መሰረት ከት/ቤት እገዳ የማድረግ ደንቦቹ በትክክል መተግበራቸውን ለማረጋገጥ የርእሰመምህሩን ውሳኔ እንዲገመግም የተማሪዎች ድጋፍ እና ክትትል አገልግሎት ክፍል ዳይሬክተርን (DSSAS) ሊጠይቁ ይችላሉ። DPPAS በሚሰጠው ውሳኔ ካልረኩ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች 15 ቀናት ውስጥ የተማሪ ስነምግባር እና ይግባኝ ሰሚ ክፍልን በማነጋገር ወደ ሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

የተራዘሙ እገዳዎች ወይም ከት/ቤት መባረር (ከ10 ቀናት በላይ) ለማባረር የወሰኑት ርእሰ መምህሩ ከሆኑ፣ ሁኔታው እንደገና እንዲታይ የመጠየቅ ሂደቱ ትንሽ የተለየ ነው። ማንኛውም ተማሪን ለ10 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ የማገድ ውሳኔ በተማሪዎች የስነምግባር እና ይግባኝ ሰሚ ክፍል በኩል መጠየቅ አለበት። ተማሪን የማባረር ውሳኔው የተሰጠው ከሱፐርኢንተንደንቱ ከሆነ፣ ወላጅ/አሳዳጊ የሱፐርኢንተንደንቱ ውሳኔ ባለው መረጃ መሠረት ህጎቹን መሰረት ያላደረገ ስህተት መሆኑን ካመኑ፣10 ቀናት ውስጥ በቀጥታ ለትምህርት ቦርድ ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

አንድ ተማሪ በዲሲፕሊን እርምጃ ምክንያት በተለዋጭ የትምህርት መርሃ ግብር ከተመደበ(ች)፣ እንደ ቆይታው ሁኔታ ረዘም ያለ እገዳ ወይም መባረር እንደሆነ ይቆጠራል።

ይግባኙ ከተወሰነው የእገዳ ጊዜ በላይ ሊቆይ እንደሚችል ልብ ይሏል።

### የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሊታገዱ ወይም ሊባረሩ ይችላሉ?

አዎን። የተቀመጡ የአፈጻጸም ሂደቶችን በመከተል እንዲታገዱ ወይም እንዲባረሩ ስለተወሰነባቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የፌዴራል ህጉ የህጋዊ አፈፃጸም መብቶችን ያስቀምጣል። እነዚህ መብቶች MCPS ደንብ JGA-RC፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ማገድ እና ማባረር በሚለው ላይ ሙሉ በሙሉ ተብራርተዋል።

አንድ ተማሪ በዲሲፕሊን እርምጃ ምክንያት በተለዋጭ የትምህርት መርሃ ግብር ከተመደበ(ች)፣ MCPS ደንብ JGA-RC፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ማገድ እና ማባረር ላይ እንደተገለጸው ካልሆነ በስተቀር የቆየ(ች)በት ጊዜ ረዘም ያለ እገዳ ወይም መባረር ተደርጎ ይቆጠራል።

# የተማሪ ባህሪያት እና የባህርይ ማስተካከል ጣልቃገብነት የምላሽ ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ እርምጃዎች (ለምሳሌ:- በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መነጋገር፣ በእስር ማገድ) | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚመራ/የተጠቆመ እና በአስተዳደር የሚደገፉ ምላሾች (ለምሳሌ:- ለማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት) | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና/ወይም ከትምህርት ቤት የማስወገድ ምላሾች (ለምሳሌ:- የተሐድሶ ተግባሮች፣ በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ማድረግ፣ በትምህርት ቤት ጣልቃ ገብነት፣ የአቻ ግልግል፣ በጊዜያዊነት ከትምህርት ክፍል ማስወገድ) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲሆኑ የማግለል ምላሽ (ለምሳሌ:- የተሐድሶ ተግባሮች፣ የካውንስሊንግ ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ እገዳ) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደራዊ ድጋፍ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለልን የሚካትቱ እና ወደሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ምላሾች (ለምሳሌ:- የተራዘመ እገዳ፣ ማባረር) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተገቢውን የባህርይ እርምት ጣልቃ ገብነት ደረጃ ለመወሰን በገጽ 6 ላይ ያሉትን "ማቅለያ" እና "የማባባስ" መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።** | | | | | | |
| **ከክፍል ማቋረጥ (101)** | ወደ ትምህርት ቤት ከደረሱ በኋላ ያለምክንያት ክፍል ውስጥ መገኘት አለመቻል።[1] | | | | | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ብቻ |
| | ት/ቤት ከደረሱ በኋላ በተከታታይ የተፈቀደ ምክንያት ሳይኖር ከክፍል መቅረት።[1;2] | | | | | |
| **ማርፈድ (102)**<br>ይመልከቱ:- MCPS ደንብ JEA-RA፣ Student Attendance/የተማሪ ክትትል | የተፈቀደ ምክንያት ሳይኖር ወደ ክፍል ወይም ወደ ት/ቤት ከአንድ ጊዜ በላይ ዘግይቶ መድረስ።[1;2] | | | | | ሁለተኛ ደረጃ ብቻ<br>የሚያረፍዱ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የከበደ ቅጣት ወይም የማግለል እርምጃ መሰጠት የለባቸውም፣ ነገር ግን ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው እንዲያውቁት መደረግ አለበት። |
| | ያለምክንያት ያለምክንያት ወደ ክፍል ወይም ትምህርት ቤት ዘግይቶ መድረስ።[1,2] | | | | | |
| **ውስልትና/ዋልጌነት (103)**<br>MCPS ደንብ JEA-RA፣ ስለ ተማሪ የትምህርት ቤት መከታተል ይመልከቱ | ባልተፈቀደ ምክንያት ከት/ቤት መቅረት።[1; 2] | | | | | በህጋዊም ሆነ በህገ-ወጥ መንገድ ከመጠን በላይ መቅረት እና/ወይም ዘግይቶ መምጣት የሚያዘወትሩ ተማሪዎች ወደ የተማሪ ደህንነት ቡድን (SWBT) ሊላኩ ይችላሉ። SWBTs ለተደጋጋሚ መቅረት ዋና መንስኤ እና መደበኛ ክትትልን ለመጨመር የተነደፉ ተገቢ ጣልቃገብነቶችን የመወሰን ሂደት ይተገብራል። በተደጋጋሚ መቅረት ስለሚያበዙ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጆቻቸውን የትምህርት ቤት ክትትል ሁኔታ በተመለከተ በመደበኛነት እንዲያውቁ ይደረጋ። |
| | ወስላታነት/ዋልጌነት[3] | | | | | |

[1]አንድ ተማሪ "ት/ቤት አለመገኘት ጋር በተያያዙ ጉድለቶች ምክንያት ብቻ" ከት/ቤት ሊታገድ ወይም ከት/ቤት ሊሰናበት አይችልም። ሜሪላንድ (MD) ANN. CODE, EDUCATION § 7-305. ይህ በዚህ ገፅ ላይ ለተዘረዘሩት ከክፍል መቅረት፣ መዘግየት፣ እና የዋልጌነት ስነምግባሮች ተግባራዊ ይደረጋል።

[2] የመቅረት ፈቃድ የሚያሰጡ ምክንያቶች:- ቤተሰብ ውስጥ የሚያጋጥም ሞት፣ የተማሪዋ(ው) ወይም የተማሪዋ(ው) ልጅ ህመም፣ እርግዝና፣ እና ከወላጅነት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች፣ የፍርድ ቤት ቀጠሮ፣ አደገኛ የአየር ሁኔታዎች፣ ሃይማኖታዊ በዓልን ለማክበር፣ የስቴቱ ድንገተኛ ሁኔታ፣እገዳ፣ትምህርት ቤቱ ስፖንሰር ያደረገው እንቅስቃሴ፣ እና MCPS ደንብ JEA-RA፣ የተማሪዎች በትምህርት ላይ ስለመገኘት ደንብ ላይ የተገለጹ ሌሎች ሁኔታዎች፥COMAR። 13A.08.01.03.

[3]አንድ ተማሪ በማንኛውም ሩብ አመት ከ 8 ቀኖች በላይ፣ በአንድ ሴሚስተር 15 ቀኖች፣ ወይም በትምህርት አመት ውስጥ 20 ቀኖች "ከትምህርት ቤት ሳያስፈቅድ መቅረት" (በግምት 10%) ያለፈቃድ መቅረት ነው። ሜሪላንድ (MD) ANN.CODE, EDUCATION § 7-355.



# የተማሪ ባህሪያት እና የባህርይ ማስተካከል ጣልቃገብነት የምላሽ ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ እርምጃዎች (ለምሳሌ:- በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መነጋገር፣ በእስር ማገድ) | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚመራ/የተጠቆመ እና በአስተዳደር የሚደገፉ ምላሾች (ለምሳሌ:- ለማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት) | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና/ወይም ከትምህርት ቤት የማስወገድ ምላሾች (ለምሳሌ:- የተሐድሶ ተግባሮች፣ በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ማድረግ፣ በትምህርት ቤት ጣልቃ ገብነት፣ የአቻ ግልግል፣ በጊዜያዊነት ከትምህርት ክፍል ማስወገድ) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲሆኑ የማግለል ምላሽ (ለምሳሌ:- የተሐድሶ ተግባሮች፣ የካውንስሊንግ ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ እገዳ) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደራዊ ድጋፍ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለልን የሚካትቱ እና ወደሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ምላሾች (ለምሳሌ:- የተራዘመ እገዳ፣ ማባረር) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተገቢውን የባህርይ እርምት ጣልቃ ገብነት ደረጃ ለመወሰን በገጽ 6 ላይ ያሉትን "ማቅለያ" እና "የማባባስ" መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።** | | | | | | |
| **ንቀት፣አለማክበር**<br>*አለመታዘዝ ከንቀት፣አለማክበር ጋር ተጠቃልሏል። | ተገቢ ያልሆኑ ወይም ጎጂ የማፌዝ ምልክቶች፣ በቃል ወይም በፅሁፍ የሚገለጹ አስተያየቶች፣ ወይም ለሌሎች የሚያሳዩት ስነምግባር (ለምሳሌ:- የቃል ስድብ፣ መራገም፣ መላልሶ መጨቃጨቅ)። | | | | | የማያቋርጥ እና ልምድ ከሆነ እናም ስነምግባሩ በትምህርት ላይ ተጽእኖ ካደረገ ንቀት፣አለማክበር እንደ ረብሻ ሊቆጠር ይችላል። |
| | የመምህራንን፣ የሰራተኞችን፣ ወይም የአስተዳዳሪዎችን መመሪያዎች በተደጋጋሚ መቃወም ወይም አለመቀበል። | | | | | |
| **ረብሻ (704)** | የትምህርት አካባቢን ሰላም በሚነሳ ተግባር መሳተፍ። | | | | | |
| | | 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች | | | | |
| | መማር እና ማስተማርን በሚያደናቅፍ እና በቀጥታ የሌሎችን ደህንነት በሚያሰጋ ሁኔታ ከመለስተኛ እስከ ከባድ ተግባር ላይ መሳተፍ። | | | | | |
| | | | | 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች | | |
| | | | በሰዎች ወይም በንብረት ላይ አደጋ መፍጠር፣ ወይም ቀጣይነት ያለው የትምህርት ሂደቱን የማስተጓጎል ስጋት መፍጠር። | | | |
| | | | 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች | | | |
| | ጥላቻን ወይም መድልዎን የሚያበረታታ ቋንቋን መጠቀም ወይም ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን መንዛት በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ስራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ያስከትላሉ ተብሎ ይታመናል። የቦርድ ፖሊሲ ACA፣ ፀረ መድሎአዊነት፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ይመልከቱ። | | | | | |

# የተማሪ ባህሪያት እና የባህርይ ማስተካከል ጣልቃገብነት የምላሽ ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ እርምጃዎች (ለምሳሌ፦ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መነጋገር፣ በእስር ማገድ) | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚመራ/ የተጠቆመ እና በአስተዳደር የሚደገፉ ምላሾች (ለምሳሌ፦ ለማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት) | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና/ወይም ከትምህርት ቤት የማስወገድ ምላሾች (ለምሳሌ፦ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ማድረግ፣ በትምህርት ቤት ጣልቃ ገብነት፣ የአቻ ግልግል፣ በጊዜያዊነት ከትምህርት ክፍል ማስወገድ) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲሆኑ የማግለል ምላሽ (ለምሳሌ፦ የተሐድሶ ተግባሮች፣ የካውንስሊንግ ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ እገዳ) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደራዊ ድጋፍ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለልን የሚካትቱ እና ወደሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ምላሾች (ለምሳሌ፦ የተራዘመ እገዳ፣ ማባረር) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተገቢውን የባህርይ እርምት ጣልቃ ገብነት ደረጃ ለመወሰን በገጽ 6 ላይ ያሉትን "ማቅለያ" እና "የማባባስ" መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።** | | | | | | |
| **ተገቢ ያልሆነ የግል ኤሌክትሮኒክስ መገልገያ አጠቃቀም (802)[4]**<br>MCPS እነዚህን "የግል ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች" ወይም "PMDs" ይላቸዋል።<br>MCPS ደንቦችን ይመልከቱ፦- COG-RA የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች፣ IGT-RA፣ ለኮምፒውተር ሲስተም፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ፣ እና አውታረ መረብ አጠቃቀምን በሚመለከት የተጠቃሚ ኃላፊነቶች፦-<br>ደህንነት፣ ILA-RA፣ ስለ ደህንነት እና ሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶች የተደረጉ ግምገማዎች | የ MCPS እና የ PMDs ደንቦችን በመጣስ የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያን መጠቀም[4,5] | | | | | ከ MCPS ንብረት የራቀ ሥፍራ ላይ የስነምግባር ጉድለት ከት/ቤት መቼት ጋር ግንኙነት ሲኖረው፣የትምህርት አካባቢው በአካልም ሆነ ቨርቹዋል ቢሆንም፣ ባህሪው በትምህርት ቤት እያሉ ሌሎች ተማሪዎችን የመጉዳት አደጋ ሲፈጥር፣ወይም ምግባሩ በትምህርት አካባቢ ላይ የማደናቀፍ ድርጊት የሚያስከትል ከሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል። |
| | | ተማሪ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው/ከተሰጣት በኋላ MCPS ደንብ በመጣስ የግል ተንቀሳቃሽ/ሞባይል መሳሪያ መጠቀም ወይም | | | | |
| | | | 6ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች | | | |
| | | የሌሎችን ግላዊነት የሚጥስ PMD በመጠቀም መረጃን ማስተላለፍ፣ የተማሪዎችን ወይም የሰራተኞችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ መጣል፣ ጸያፍ ንግግር ወይም ስድብ፣ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ወይም MCPS ስራዎችን እንዲደናቀፍ ማድረግ፣ የአካዳሚክ ታማኝነት የጎደለው ድርጊት መፈፀም፣ ወይም MCPS የኮምፒዩተር ሲስተሞችን፣ ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎችን፣ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን (የትምህርት ውጤቶችን ወይም ሌላ የተማሪ መረጃዎችን ጭምር) ደህንነታቸውን በመጣስ አደጋና ስጋት መፍጠር። | | | |
| | | | | PMD እና MCPS አውታረመረብ ወይም ኦፕሬሽኖች ላይ መስተጓጎል በሚፈጥር መልኩ፣ PMD በመጠቀም ሪኮርዶችን መቀየር፣ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ንብረትን ማጥፋት፣ ወይም MCPS ንብረት የሆነ መሳሪያን ከውጫዊ ፕሮክሲ ወይም ቨርቹዋል የመረጃ መንታፊ ጋር በማጣመር የሞንትጎምሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውታረመረብ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ለማበላሸት መሞከርን ጭምር ያጠቃልላል። | | |
| **የአለባበስ ሥርዓት/ኮድ (706)**<br>MCPS ደንብ JFA-RA፥ የተማሪ መብቶችና ሀላፊነቶች | ማስጠንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ የአለባበስ ስርአት የሚጥስ/የምትጥስ ተማሪ። | | | | | |
| | ማስጠንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ የአለባበስ ስርአት ደጋግሞ የሚጥስ/የምትጥስ ተማሪ። | | | | | |

[4]PMD ሶስት መለያ ባህሪያት አሉት፦- 1) MCPS የመሳሪያው ባለቤትነት የለውም ወይም አልሰጠም። 2) መሳሪያው መረጃን ለመላክ እና ለመቀበል የኢንተርኔት፣ wi-fi ወይም ሴሉላር ግንኙነት የማግኘት፣የመቀበል፣ የማስተላለፍ አቅም ካለው። 3) መሳሪያው ድምጽ እና ምስሎችን/ቪዲዮ የመቅረጽ አቅም ካለው።

[5] የሌሎች የንግድ ማስታወቂያ የሌሎችን ግላዊነት የሚጥስ መረጃ ከሆነ፣የተማሪዎችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል፣ብልግና ወይም ስድብ ከሆነ፣የትምህርት ቤት የሥራ እንቅስቃሴዎችን የሚያበላሽ ከሆነ፣ ስራን የሚያስተጓጉል ከሆነ የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያ (PMD) በመጠቀም ሊተላለፍ አይገባም።



# የተማሪ ባህሪያት እና የባህርይ ማስተካከል ጣልቃገብነት የምላሽ ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ እርምጃዎች (ለምሳሌ፦ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መነጋገር፣ በእስር ማገድ) | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚመራ/ የተጠቆመ እና በአስተዳደር የሚደገፉ ምላሾች (ለምሳሌ፦ ለማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት) | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና/ወይም ከትምህርት ቤት የማስወገድ ምላሾች (ለምሳሌ፦ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ማድረግ፣ በትምህርት ቤት ጣልቃ ገብነት፣ የአቻ ግልግል፣ በጊዜያዊነት ከትምህርት ክፍል ማስወገድ) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲሆኑ የማግለል ምላሽ (ለምሳሌ፦ የተሐድሶ ተግባሮች፣ የካውንስሊንግ ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ እገዳ) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደራዊ ድጋፍ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለልን የሚካትቱ እና ወደሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ምላሾች (ለምሳሌ፦ የተራዘመ እገዳ፣ ማባረር) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ተገቢውን የባህርይ እርምት ጣልቃ ገብነት ደረጃ ለመወሰን በገጽ 6 ላይ ያሉትን "ማቅለያ" እና "የማባባስ" መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።** | | | | | | |
| **አልኮሆል (201)**<br>የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ MCPS ውስጥ አልኮሆል፣ትምባሆ፣ እና ሌሎች አደንዛዥ እጾችን አላግባብ መጠቀምን ስለመከላከል፣ የሞንትጎምሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች፦- COF-RA፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌላ<br>MCPS ንብረት ላይ አደንዛዥ እፆችን እና IGO-RA፣ ተማሪዎችን የሚያካትቱ የአልኮል፣የካናቢስ፣ትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ክስተቶችን የሚመለከቱ መመሪያዎች | | | በአልኮል ተጽእኖ ስር መውደቅ።[6፣8] | | | እንደ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካል፣ ትምህርት ቤቱ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ወይም MCPS የመከላከል እና የህክምና ፕሮግራም መምራት አለበት። |
| | | | አልኮል መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት[6,8] | | | |
| | | | አልኮል ማሰራጨት/መሸጥ።[7] | | | |
| **በትንፋሽ የሚሳቡ እፆች/ INHALANTS (202)[8]**<br>የቦርድ ፖሊሲ IGN፣ MCPS ውስጥ አልኮል፣ትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አላግባብ መጠቀምን ስለ መከላከል፦- MCPS ደንቦች፣ COF-RA፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌላ<br>MCPS ንብረት ላይ መድሃኒቶችን፣ እና IGO-RA፣ ተማሪዎችን የሚያካትት የአልኮል፣ የካናቢስ፣ የትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ክስተቶችን የሚመለከቱ መመሪያዎች | | | በትንፋሽ በመሣብ የሚወሰዱ እፆች ተጽእኖ ስር መውደቅ።[6፣8] | | | እንደ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካል፣ ትምህርት ቤቱ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ወይም MCPS የመከላከል እና የህክምና ፕሮግራም ማስተላለፍ አለበት። |
| | | | አደንዛዥ እፆችን በትንፋሽ መሳብ/ማሽተት እና ይዞ መገኘት[6,8] | | | |
| | | | በትንፋሽ በመሣብ የሚጤሱ እፆችን ማሰራጨት/መሸጥ[7,9] | | | |

[6]ተማሪው(ዋ) አልኮል፣ አደገኛ ዕጾችን በመጠቀም በድንዛዜ ላይ ከተገኘ(ች) እና ትምህርት ቤት ውስጥ የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ከሌለ፥ ተማሪው(ዋ)ን ወደ ቤት መላክ እና ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ወይም ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ክፍል ማስተላለፍ አስፈላጊ ይሆናል። ተማሪው(ዋ)ን ወደ ቤት ከመላክ በፊት፣ተማሪው(ዋ) የት/ቤቱን ግቢ ሲለቅ/ስትለቅ በአንድ የቤተሰብ አባል ወይም ለመርዳት በሚችል ግለሰብ መታጀቡን/መታጀቧን ለማረጋገጥ ት/ቤቱ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል። MCPS ፖሊሲ IGN በሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ት/ቤቶች ውስጥ የአልኮል፣የትምባሆ፣እና የሌሎች ጎጂ መድሃኒቶችን ህገ-ወጥ አጠቃቀምን መከላከል በተጨማሪ ይመልከቱ።

[7]የት/ቤት ስነስርአት የማስከበር ጉዳይን በሚመለከት፣ አልኮል፣ በትንፋሽ እየተሳበ የሚጤሱ መድሀኒቶች/የተከለከሉ እፆችችን ስርጭት፣ ሽያጭ ወይም የመሸጥ አዝማምያ መከላከል።

[8]ለመረጃ ያክል፣ የአካል ጉዳተኝነት ላላቸው ተማሪዎች ብቻ፡ በኮድ 892 ተጠቀሙ። (ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች "የህገወጥ እፆች" ትርጉም በህጋዊ መንገድ ያልተገኙ ነገሮች፣ ህጋዊ ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ ቁጥጥር ብቻ አገልግሎት ላይ የሚውል፣ ወይም ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው መዳኒቶች አጠቃቀም ደንብ ወይም በሌላ የፌደራል ህግ እውቅና በተሰጠው ባለስልጣን ቁጥጥር አገልግሎት ላይ የሚውል ማለት ነው።)

[9]ለመረጃ አያያዝ እንዲያመች፣ የአካል ጉዳት ላላቸው ልጆች ብቻ፣ 21 U.S.C. § 812; 21 C.F.R. pt. 1308 ቁጥጥር የሚደረግባቸው መዳኒቶች ዝርዝሮች ውስጥ የተለዩ እፆችን ስለመሸጥ በኮድ ቁጥር 891 ይጠቀሙ።

## የተማሪ ባህሪያት እና የባህርይ ማስተካከል ጣልቃገብነት የምላሽ ደረጃዎች

| አስተዳደር | ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡- በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መነጋገር፣ በእስር ማገድ) | ደረጃ 2<br>በአስተማሪ የሚመራ/የተጠቆመ እና በአስተዳደር የሚደገፉ ምላሾች (ለምሳሌ፡- ለማህበረሰብ አገልግሎት መስጠት) | 3ኛ ደረጃ<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና/ወይም ከትምህርት ቤት የማስወገድ ምላሾች (ለምሳሌ፡- የተሐድሶ ተግባሮች፣ በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ማድረግ፣ በትምህርት ቤት ጣልቃ ገብነት፣ የአቻ ግልግል፣ በጊዜያዊነት ከትምህርት ክፍል ማስወገድ) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደር የሚደገፉ እና ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲሆኑ የማግለል ምላሽ (ለምሳሌ፡- የተሐድሶ ተግባሮች፣ የካውንስሊንግ ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ እገዳ) | ደረጃ 5<br>በአስተዳደራዊ ድጋፍ ለረጅም ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለልን የሚካትቱ እና ወደሚመለከተው አካል የማስተላለፍ ምላሾች (ለምሳሌ፡- የተራዘመ እገዳ፣ ማባረር) | መወሰድ ያለበትን እርምጃ ደረጃውን ለመወሰን ዓውዱን እና ምክንያቶቹን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተገቢውን የባህርይ እርምት ጣልቃ ገብነት ደረጃ ለመወሰን በገጽ 6 ላይ ያሉትን "ማቅለያ" እና "የማባባስ" መመዘኛዎችን ግምት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። | | | | | | |
